የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ ሐምሌ ፱ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 44
ADDIS ABABA, 16th July, 2024

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፶፪/፪ሺ፲፮

የቤተ-መንግስት አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……..……………………….……..….ገጽ ፲፭ሺ፯፻፲፪

## Content

Regulation No 552/2024

Palace Administration Council of Ministers Regulation ………...……..…... Page 15712

**ደንብ ቁጥር ፭፻፶፪/፪ሺ፲፮**

**የቤተ-መንግስት አስተዳደር ለመደንገግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በቤተ-መንግስት አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፶፱/፩ሺ፱፻፺፯ አንቀጽ ፲፪ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የቤተ-መንግስት አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቀጥር ፭፻፶፪/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የመስተንግዶ አገልግሎት**

የቤተ-መንግስት አስተዳደሩ ፡-

፩/ መንግስት በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የመስተንግዶ አገልግሎት ያስተባብራል፤ ያስፈፅማል፡፡

፪/ በሥራ ላይ ለሚገኙ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ፕሬዚዳንት እና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የመኖሪያ ቤት መስተንግዶ አገልግሎት ይሰጣል ፤ ይህንን የሚያስተባብር የሰው ኃይል ይመድባል፡፡

**Regulation No 552/2024**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR PALACE ADMINISTRATION**

This Regulation is issued by Council of Ministers pursuant to Article 12 of the palace Administration Establishment Proclamation No. 459/2005.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Palace Administration Council of Ministers Regulation No. 552/2024".

**2. Reception Service**

The Palace Administration shall:

1/ Coordinate; execute reception services according to government orders.

2/ Renders residential accommodation service to the Prime Minister, the Deputy Prime Minister and arrange office for the President and assign such personnel that coordinate the same.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የጠቅላይ ሚኒስትር፣ የፕሬዝዳንት እና የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር መኖሪያ ቤት ያደራጃል፣የመገልገያ ዕቃዎችን ያሟላል፣ ይጠግናል፣ ያስተዳድራል፤ የፕሬዝዳንቱን ቢሮ ያደራጃል፡፡

፬/ በመንግስት በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የሀገር መሪዎች የሚስተናገዱበት ደረጃቸውን የጠበቁ የፕሮቶኮል ተሽከርካሪዎች ስምሪት እና የመስተንግዶ አገልግሎት ይሰጣል፣ይከታተላል፣ ያስተዳድራ፡፡

## ፫. <u>የገቢ ማስገኛ ስራዎች</u>

፩/ የቤተ-መንግስት አስተዳደሩ የሚከተሉትን የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ያከናዉናል፡-

ሀ) በተለያየ ቦታ የሚገኙ የቤተ-መንግስት ቅርሶችን በተለያየ መንገድ ከውጭና ከሀገር ውስጥ በመሰብሰብና በእጅ ላይ የሚገኙ ቅርሶችን አደራጅቶ ለዕይታ ማቅረብ፤

ለ) ከቤተ-መንግስት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የስጦታ ዕቃዎች በማሳተም ወይም በማሰራት ለሽያጭ ማቅረብ፤

ሐ) የግብርና ሥራዎችን በማከናወን ምርትን ለገበያ ማቅረብ፤

መ) የከተማ ውስጥ የሠረገላ አገልግሎት፣ የፈረስ ስፖርት ውድድር፣ የሠለጠነ ፈረስ በመሸጥ፣ በፈረስ ኪራይ አገልገሎት፣ ፈረስ ለግልቢያ በማሰልጠን እና ሌሎች የመዝናኛ አገልግሎት መስጠት፤

ሠ) በቤተ-መንግስት አስተዳደር ብቻ የሚዘጋጁ ልዩ የምግብ፣ የመጠጥ እና የመስተንግዶ አገልግሎት መስጠት፤

ረ) ለንግድ ሥራ የሚያገለግሉ የተለያዩ ቤቶችን በማከራየት እና የሪዞርት አገልግሎት መስጠት፤ እንዲሁም

3/ Without prejudice to Sub Article 2 of this Article, organizes, supplies, repairs and manages the residences of the Prime Minister, President and Deputy Prime Minister; organizes the office of the President.

4/ Provide, follow up and administer Protocol Vehicles and reception service to Heads of States following direction issued from government.

## 3. <u>Income Generation</u>

1/ The Palace administration may carry out the following income generating activities:

a) Collecting Articles of cultural heritage belonging to the palace from abroad and domestically, and organizes and displays these Heritages;

b) Offering for sale gift items related to the palace by printing or Making;

c) Carrying out agricultural activities and sale the product;

d) Carriage service in the city, horse sports competitions, selling trained horses, horse rental services, training horses for riding and providing other entertainment services;

e) Provide special food, beverage and reception services exclusively produced by the palace Administration;

f) Renting various houses for business and providing resort services;

ሰ) የተፈጥሮ ፍል ውሃ አገልገሎት በመስጠት ገቢ ማመንጨት ናቸው፡፡

፪/ አስተዳደሩ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚያስከፍለውን ክፍያ መጠን በተመለከተ ተጠሪ ለሆነው አካል እያቀረበ የሚያስወስን ይሆናል፡፡

**፬. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>**

፩/ በልዩ የመንግስት ውሳኔ ካልሆነ በስተቀር የቤተ-መንግስት ቅርሶችንና መዛግብትን በንግድ ምልክት ማስመዝገብ፣ መሸጥ፣ በስጦታ ወይም በውርስ እንዲሁም በማንኛውም መንገድ ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፣

፪/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገዉን ተላልፎ የተገኘ ማንኛዉም ሰዉ አግባብ ባለዉ የወንጀል እና የፍትሐብሄር ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፭. <u>ተፈፃሚነት የሌላቸዉ ደንቦችና ልምዶች</u>**

ከዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፮. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፱ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

g) Income derived from providing natural spa services.

2/ Prepares and submits the service fees for approval to the Council of Ministers.

**4. <u>Prohibited Activities</u>**

1/ It is prohibited to register, sell, gift or inherit palace cultural Heritages and treasuries as a trademark, or transfer them in any way, except by special Government decision.

2/ Any person who violates the provisions of Sub Article 1 of this Article shall be liable under the relevant Criminal and Civil laws.

**5. <u>Inapplicable Laws</u>**

Any Regulation or Customary Practice contrary to the provisions of this Regulation shall not be applicable on matters covered by this Regulation.

**6. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 16th Day of July,2024**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**